# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## የተሳሳፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ

መ. ቁ. 16

# የተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 16/2001

የገቢ፣ ወጪ እና ተላላፊ ዕቃዎችን የጉዞ መተላለፊ መንገድ በሕግ መወሰንና ከተወሰነው መንገድ ውጭ የሚጓጓዙ፣ የሚቆሙ፣ የሚያራግፉና የሚጭኑ አጓጓዦችን ለመቆጣጠር እና ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ በማስፈለጉ፤

በገቢ፣ በወጪና በተላላፊ ዕቃዎች ላይ አገሪቷ ማግኘት የሚገባትን ገቢ በአግባቡ እንዲሰበሰብ ለማድረግ፣ የመተላለፊያ መንገዶች ላይ በሚደረገው የቁጥጥር ስራ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት ኃላፊነትና ግዴታ በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 622/2001 አንቀጽ 19(3) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 16/2001 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣

1. **"ተላላፊ ዕቃ"** ማለት ማጓጓዣ በመቀየር ወይም በመጣበት ማጓጓዣ በተፈቀደ የመተላለፊያ መሥመር የኢትዮጵያን ግዛት አቋርጦ የሚሄድ ወይም ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ የሚንቀሳቀስ ዕቃ ነው፡፡

2. **"የጉምሩክ ትራንዚት ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም"** ማለት ተላላፊ ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ሆነው ከጉምሩክ ትራንዚት መነሻ እስከ መድረሻ ቦታ የሚተላለፉበት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ሂደት ነው፡፡

3. **"የመተላለፊያ መሥመር"** ማለት በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ያሉ ገቢና ወጪ ዕቃዎች የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ወደሚያጠናቅቁበት ሥፍራ እንዲጓጓዙበት በባለሥልጣኑ የተወሰነ ማናቸውም መንገድ ነው፡፡

4. **"የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አስፈፃሚ "** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 2(15) የተሰጠውን ትርጓሜ የሚይዝ ሆኖ የጉምሩክ ተላላፊ ዕቃዎችን የሚያስተላልፍ ሰው ነው፡፡

5. **"የጉምሩክ ማሸጊያ"** ማለት ባለሥልጣኑ በሚያወጣው የሕዝብ ማስታወቂያ የሚገለጽ እና የተላላፊ ዕቃዎች መያዣ ወይም ማጓጓዣ ላይ የተጫነ ዕቃ የሚታሸግበት ወይም የሚታሰርበት መሳሪያ /ዲቫይስ/ ነው፡



111

6. "ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ" ማለት አጓጓዡ በጉምሩክ ትራንዚት ኦፐሬሽን ወቅት ተላላፊ ዕቃን ለጉምሩክ ትራንዚት ኦፐሬሽን በተፈቀደለት የጊዜ ገደብ እና ሁኔታ የትራንዚት መድረሻው ቦታ ላይ እንዳይደርስ እክል ሊሆን የሚችል እና አግባብ ባለው ህግና በአለም አቀፍ ስምምነት ተቀባይነት ያለው ከአጓጓዡ ቁጥጥር ውጪ የሆነ ክስተት ነው፡

7. "ከአቅም በላይ ለሆነ ሁኔታ የሚቀርብ ማሥረጃ" ማለት በጉምሩክ ትራንዚት ስነ-ስርዓት አፈፃፀም ወቅት ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ የገጠመው አጓጓዥ ሁኔታውን በአቅራቢያው ለሚገኝ የባለሥልጣኑ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ወይም ህግ አስከባሪ አካል አስታውቆ ከዚሁ አካል የተሰጠው ስለ ሁኔታው የሚገልጽ የጽሁፍ ማረጋገጫ ነው።

8. "ፖትሮሊንግ" ማለት ወደ ሀገር ለመግባት ወይም ከሀገር ለመውጣት የትራንዚት ፈቃድ ያገኙ፤ እንዲሁም ከወደብ እና መግቢያ በሮች የሚንቀሳቀሱ ተላላፊ ዕቃዎችን መረጃ በማጠናቀር አስቀድሞ በተነደፈ መርሐ - ግብር መሠረት በመተላለፊያ መሥመሮች ላይ በፌደራል ፖሊስ እና/ወይም በባለሥልጣኑ መ/ቤት የሚደረግ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ነው።

9. "የጉምሩክ ጣቢያ"፣ "የጉምሩክ ወደብ" እና "የማጓጓዣ ኃላፊ" በአዋጁ የተሰጣቸውን ትርጓሜ ይይዛሉ።

10. "አዋጅ" ማለት የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 622/2001 ነው።

11. " ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ነው።

3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማ የጉምሩክ ተላላፊ ዕቃ ሥነ-ሥርዓት በመፈፀም ወደ ሀገር በሚገቡ፣ ከሀገር በሚወጡ፣ አገር አቋርጠው በሚሄዱ ወይም በአገር ውስጥ በሚተላለፉ ዕቃዎች ላይ የሚፈፀሙ፤-

- ❖ ከተፈቀደው መግቢያና መውጫ የጉምሩክ በር የመውጣት፣
- ❖ ከተፈቀደው የመተላለፊያ መስመር የመውጣት፣
- ❖ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ ያለመድረስ፣
- ❖ የጉምሩክ እሽጐችን የመፍታት፣ ወይም የመስበር፣
- ❖ በማጓጓዣ ላይ የተጫኑ ተላላፊ ዕቃዎችን ከጉምሩክ ዕውቅናና ፈቃድ ውጪ የማራገፍ ወይም የመጫን ወይም የመቀላቀል ወይም የማጉደል፣
- ❖ የዕቃዎቹ የመተላለፊያ ሰነድ የመሰረዝ የመደለዝ እና ሌላ ተገቢ ያልሆኑ ህገወጥ ተግባሮችን በመከላከል በወጪና በገቢ ንግዱ ላይ ሊፈጠር የሚችልን ጉዳት ተፅዕኖ መቀነስ፣ መከላከልና አጥፊዎችንም ለሕግ በማቅረብ ተገቢው ህጋዊ የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ማስቻል ነው፡፡

4. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ወደ ሀገር በሚገቡ ፣ ከሀገር በሚወጡ፣ አገር አቋርጠው በሚሄዱ እና በአገር ውስጥ በሚንቀሳቀሱ ተላላፊ ዕቃዎች፣ ማጓጓዣዎች፣ ከእነዚሁ ጋር ግንኙነት ባላቸው አስተላላፊዎች፣ አጓጓዦች እና ሌሎች ሰዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለ ተላላፊ ዕቃዎች</u>

5. <u>ጠቅላላ</u>

   1. ማናቸውም በተላላፊነት የተመዘገበ ዕቃ እንቅስቃሴውን ከመጀመሩ በፊት የተላላፊነት የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ይፈፀምበታል፡፡
   2. ተላላፊ ዕቃዎች በባለሥልጣኑ በተወሰነው የጉምሩክ ወደብ በኩል በመግባት በተፈቀዱ የመተላለፊያ መስመሮች ዋናውን መንገድ ብቻ ተከትለው መጓጓዝ ይኖርባቸዋል፡፡



113

3. ማናቸውም ተላላፊ ዕቃ እንቅስቃሴው በሚያበቃበት የጉምሩክ ወደብ በባለሥልጣኑ በተወሰነው ጊዜ እና ከጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ በተላከበት ሁኔታ መድረስ ይኖርበታል፡፡

6. <u>ስለተላላፊ ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ እና መድረሻ ቦታዎች</u>

1. ወደ ሀገር ለሚገቡ ተላላፊ ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ የሚሆኑት የጉምሩክ መግቢያ በሮች ፤
   - ሀ. በጅቡቲ በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ጋላፊ እና ደወሌ፣
   - ለ. በሱዳን በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ሁመራ፣ መተማ ዮሐንስ፣ ጋምቤላ ፣ማንኩሽ እና ኩምሩክ፣
   - ሐ. በኬንያ በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ሞያሌ፣ ኦሞራቴ
   - መ. በሶማሌ በኩል ለሚገቡ ዕቃዎች - ቶጐጫሌ፣ እንዲሁም
   - ሠ. ባለሥልጣኑ የሚሰይማቸው ሌሎች መግቢያ በሮች ናቸው፡፡
2. ወደ ሀገር ለሚገቡ ተላላፊ ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መድረሻ ቦታ የሚሆኑት፤
   - ሀ. በመሐል ሀገር የሚገኝ የጉምሩክ ጣቢያ፣
   - ለ. ፈቃድ የተሰጠው የጠቅላላ ወይም የግል ዕቃ ማከማቻ መጋዘን፣
   - ሐ. የተፈቀደ የተላላፊ ዕቃ ማራገፊያ ቦታ፣
   - መ. ባለሥልጣኑ የሚሰይመው የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ጽ/ቤት እንዲሁም በሚመለከተው አካል የሚወሰኑ የደረቅ ወደቦች ናቸው፡፡
3. ወደ ውጭ አገር ለሚወጡ ተላላፊ ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ ተደርገው የሚቆጠሩት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት የጉምሩክ ትራንዚት መድረሻ ቦታዎች ናቸው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተዘረዘሩት የጉምሩክ መግቢያ በሮች፤ ወደውጭ አገር ለሚወጡ ተላላፊ እቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መድረሻ ቦታዎች ተደርገው ይቆጠራሉ፡፡



114

7. <u>በሀገር ውስጥ የሚተላለፉ ዕቃዎች</u>

በሀገር ውስጥ ለሚተላለፉ ዕቃዎች የጉምሩክ ትራንዚት መነሻ እና መድረሻ ቦታ ተደርገው የሚቆጠሩት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2) የተዘረዘሩት የጉምሩክ ትራንዚት መድረሻ ቦታዎች ናቸው፡፡

8. <u>የመተላለፊያ መስመሮች፣ የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች እና ለእንቅስቃሴው የተፈቀደ ጊዜ</u>

ወደ ውጭ ለሚላኩ ወይም ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ለተላላፊ ዕቃዎች የመተላላፊያ መስመር ተብለው የሚቆጠሩት፤

1. በጅቡቲ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ ተላላፊ ዕቃዎች፡-

**ሀ. የመተላለፊያ መስመር የሚሆነው፡-**

- ጋላፊ --- ሰመራ --- ሚሌ --- /ገዳማይቱ/-- ገዋኔ--- አዋሽ መተሐራ ----- አዳማ ----- ሞጆ--- አዲስ አበባ
  ↘ ሐዋሳ

- ጋላፊ -- ሰመራ - ሚሌ--- ጭፍራ - ወልዲያ- አላማጣ- መቀሌ፣
  ወረታ → ጐንደር
  ↘ ባህርዳር

- ጋላፊ -ሰመራ- ሚሌ - ባቲ -ኮምቦልቻ

- ደወሌ --- ድሬዳዋ ---- ሐረር --- ጅጅጋ

ሆኖ ዋናውን የተፈቀደ መስመር በመከተል የሚጓጓዝ ይሆናል፡፡

**ለ. የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች**

ጋላፊ፣ ሰመራ፣ ሚሌ፣ ገዳማይቱ፣ አዋሽ፣ ሞጆ፣ ጭፍራ፣ ወልዲያ፣ ባቲ፣ ኮምቦልቻ፣ አላማጣ፣ ወረታ፣ መቀሌ፣ ጐንደር፣ ባህርዳር፣ ሐረር፣ ጅጅጋ፣ ሚኤሶ፣ ደወሌ

**ሐ. እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀን ገደብ**

- ከጋላፊ - አዲስ አበባ <u>ሦስት</u> ቀናት
- ከጋላፊ - መቀሌ/ጐንደር/ባህርደር <u>አራት</u> ቀናት

... Revenues and Customs Authority

❖ ከደወሌ - ጅጅጋ <u>ሁለት</u> ቀናት

❖ ከጋላፊ - ሐዋሳ <u>ሦስት</u> ቀናት

ናቸው፡፡

2. **በኬንያ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ፡-**

   **ሀ. የመተላላፊያ መስመር የሚሆነው**

   ❖ ሞያሌ---ሜጋ ---- ያቤሎ ---ሀገረማርያም --- ዲላ ---ሐዋሳ ---- ሻሸመኔ - ሞጆ - አዲስ አበባ

   ❖ ኦሞራቴ ---- አርባምንጭ ----- ሻሸመኔ ---- ሞጆ--- አዲስ አበባ

   ሆኖ ዋናውን መንገድ በመከተል ብቻ ይሆናል፡፡

   **ለ. የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች**

   ኦሞራቴ፣ ነገሌ ቦረና፣ ሮቤ፣ ሞጆ፣ ሀዋሳ፣ ሜጋ፣ ዶሎ አዶ፣ ሞያሌ፣ ያቤሎ

   **ሐ. እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ**

   ❖ ከሞያሌ - አዲስ አበባ <u>ሦስት</u> ቀናት

   ❖ ከኦሞራቴ --- አዲስ አበባ <u>ሦስት</u> ቀናት

3. **በሱማሌ በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከአገር ለሚወጡ**

   **ሀ. የመተላላፊያ መስመር የሚሆነው**

   ❖ ቶጎጫሌ - ጅጅጋ--ሐረር - ሚኤሶ - አዋሽ - አዳማ- ሞጆ-- አዲስ አበባ

   (ሐረር → ድሬዳዋ)

   ሆኖ ዋናውን መንገድ በመከተል ብቻ ይሆናል፡፡

   **ለ. የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች**

   ጅጅጋ፣ሐረር፣ ደወሌ፣ ቶጎጫሌ፣ ሚኤሶ፣ አዋሽ፣ አዳማ፣ ሞጆ፣ አዲስ አበባ፣

   **ሐ. እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ**

   ❖ ከቶጎ ጫሌ - ድሬዳዋ <u>ሁለት</u> ቀናት

   ❖ ከቶጎ ጫሌ - አዲስ አበባ <u>አራት</u> ቀናት

Revenues and Customs Authority



116

4. በሱዳን በኩል ወደ ሀገር ለሚገቡ ወይም ከሀገር ለሚወጡ

ሀ. የመተላለፊያ መስመር የሚሆነው

- ❖ ሁመራ - ሽሬ - መቀሌ
- ❖ መተማ ዮሐንስ፣ ጐንደር - ሽሬ - መቀሌ
  - → ባህርዳር - አዲስ አበባ
  - → ወረታ - ወልዲያ - ኮምቦልቻ
- ❖ ሁመራ - ጐንደር -ባህርዳር - አዲስ አበባ
- ❖ ማንኩሽ --- ባህርዳር ---- አዲስ አበባ
- ❖ ጋምቤላ → ጅማ - ወሊሶ - አዲስ አበባ
  - → ነቀምት - አምቦ - አዲስ አበባ
- ❖ ኩሞሩክ - አሶሳ --- ነቀምት -- አምቦ--- አዲስ አበባ

ሆኖ ዋናውን መንገድ በመከተል ብቻ ይሆናል።

ለ. መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች

ሁመራ፣ መተማ ዮሐንስ፣ ማንኩሽ፣ ጋምቤላ፣ ኩምሩክ መቀሌ፣ አዲስ አበባ

ሐ. እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ፣

- ❖ ከሁመራ- መቀሌ ሁለት ቀናት
- ❖ ከመተማ ዬሐንስ - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት
- ❖ ከሁመራ - አዲስ አበባ አራት ቀናት
- ❖ ከጋምቤላ - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት
- ❖ ከማንኩሽ - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት
- ❖ ከመተማዬሐንስ - መቀሌ ሁለት ቀናት
- ❖ ከኩምሩክ - አዲስ አበባ ሦስት ቀናት
- ❖ ከመተማ ዮሐንስ - ኮምቦልቻ ሁለት ቀናት



117

5. አገር አቋርጠው ለሚሄዱ

## ሀ. የመተላለፊያ መስመር

**በሱዳን በኩል ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ**

ሁመራ – ሽሬ--- መቀሌ --- አላማጣ --- ወልዲያ ——► ጭፍራ ---- ሚሌ ---- አዋሽ --- ሚኤሶ ---- ደንገጐ --- ጅጅጋ --- ቶጐጫሌ

ሰመራ --- ጋላፊ

ከ/ቻ --- አ.አ --- ሞጆ --- ሐዋሳ ---- ሞያሌ

መተማ ዮሐንስ --- ጐንደር --- ወረታ ——► ባህርዳር --- አ.አ – ሞጆ --- ሐዋሳ --- ሞያሌ

ወልዲያ --- ጭፍራ ---- ሚሌ --- አዋሽ --- ሚኤሶ --- ደንገጐ ---- ሐረር --- ጅጅጋ ---- ቶጐ ጫሌ

ሰመራ ---ጋላፊ

**በጅቡቲ በኩል ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ**

አዲስ አበባ – አምቦ --- ነቀምት --- ጋምቤላ --- ኩምሩክ

ጋላፊ --- ሰመራ ---- ሚሌ --- አዋሽ --- አዳማ --- ሞጆ --- ሐዋሳ --- ሞያሌ

ጭፍራ --- ወልዲያ ---- አላማጣ --- መቀሌ --- ሽሬ ----ሁመራ

ወረታ --- ጐንደር ---- መተማ ዮሐንስ

**በሱማሌ በኩል ለሚገቢ ወይም ለሚወጡ**

ቶጐጫሌ --- ጅጅጋ --- ሐረር ---- ደንገጐ ---- ድሬዳዋ

ሚኤሶ --- አዋሽ --- አዳማ --- ሞጆ --- ሐዋሳ --- ሞያሌ

ሚሌ – ጭፍራ --- ወልዲያ ---- አላማጣ ---- መቀሌ --- ሽሬ --- ሁመራ

ወረታ ---- ጐንደር --- መተማ ዮሐንስ

**በኬንያ በኩል ለሚገቡ ወይም ለሚወጡ**

ሞያሌ --- ሐዋሳ --- ሞጆ --- አ.አ --- ባህርዳር --- ጐንደር ---- መተማ ዮሐንስ

አዳማ --- አዋሽ ---- ሚኤሶ ---- ሐረር ----- ጅጅጋ ---- ቶጐጫሌ

ሚሌ ---- ሰመራ --- ጋላፊ

Revenues and Customs Authority

አሞራቴ --- አርባምንጭ--- ሻሸመኔ – ሞጆ --- አዲስ አበባ --- ባህርዳር --- ጐንደር – መተማ ዮሀንስ

አዳማ --- አዋሽ --- ሚኤሶ --- ሐረር --- ጅጅጋ --- ቶጐጫሌ

ሚሌ --- ስመራ --- ጋላፊ

ለ. መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች

የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች በእያንዳንዱ መስመር የተመለከቱት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ለ)፣ 2(ለ)፣ 3(ለ) እና 4(ለ) ላይ የተገለጹት ናቸው።

ሐ. እንቅስቃሴው የሚያበቃበት ቀነ ገደብ

- ከሁመራ ---- ጋላፊ አምስት ቀናት
- ከሁመራ --- ቶጐጫሌ ሰባት ቀናት
- ከሁመራ ---- ሞያሌ ስድስት ቀናት
- ከመተማ ዮሐንስ ---- ጋላፊ አምስት ቀናት
- ከመተማ ዮሐንስ ---- ቶጐጫሌ ሰባት ቀናት
- ከመተማ ዮሐንስ ----- ሞያሌ ስድስት ቀናት
- ከቶጐጫሌ ----- ሞያሌ ስድስት ቀናት
- ከደወሌ ---- ቶጐጫሌ ሦስት ቀናት
- ከጋላፊ ----- ሞያሌ ስድስት ቀናት

9. ክልከላ

ማንኛውም ተላላፊ ዕቃዎችን የሚያጓጉዝ አጓጓዥ ከላይ በአንቀጽ 8 ላይ ከተዘረዘሩት የተፈቀዱ የመተላለፊያ መስመሮች ወይም የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች ውጪ ማጓጓዣውን ማሳረፍ፣ ማቆም ወይም ማጓጓዝ የለበትም።

## ክፍል ሦስት

## ስለ ኃላፊነት እና ግዴታዎች

### 10.የመቆጣጠሪያ ጣቢያዎች፣ የመግቢያና መውጫ በሮች እና የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኃላፊነት

ማንኛውም የጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ፣ የመግቢያና መውጫ በር እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፡-

1. ወደ ሀገር እንዲገቡ፣ ከሀገር እንዲወጡ ወይም አገር አቋርጠው እንዲሄዱ ፈቃድ የተሰጣቸው ተላላፊ ዕቃዎች እና ማጓጓዣዎች በባለሥልጣኑ በተወሰነው የጊዜ ገደብ እና ከጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ በተነሱበት ሁኔታ ለመድረሳቸው ማረጋገጥ፤

2. የዕቃ መያዣው ወይም ማጓጓዣው የታሸገበት የጉምሩክ ማሸጊያ የተፈታ ወይም የተነሳ ወይም የተቀየረ እና ከተላላፊ ዕቃዎች ላይ ዕቃ ለመቀነስም ሆነ ለመጨመር የተደረገ ህገ-ወጥ ድርጊት ስለመፈፀሙ የሚያስረዱ ሁኔታዎች መኖራቸውን ካረጋገጡ ወይም በቂ ጥርጣሬ ካደረበት የዕቃ መያዣውን ወይም ማጓጓዣውን በራሳቸው የጉምሩክ ማሸጊያ በማሸግ በፌደራል ፖሊስ እና ወይም እንደአግባብነቱ በባለሥልጣኑ የህግ ማስከበር አባል/ኦፊሰር ታጅቦ ወደ ትራንዚት መድረሻ ጣቢያው እንዲጓጓዝ የማድረግ እና ተገቢው ህጋዊ እርምጃ መወሰዱን የመከታተል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

3. የመድረሻ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ በተገለፀው ሁኔታ የሚደርሱ ዕቃዎችን የትራንዚት ቡድንና የህግ ማስከበር የሥራ ሂደት በጋራ በዝርዝር በመፈተሽ የተገኘውን ውጤት እና የተወሰደውን እርምጃ ለሚመለከተው የመቆጣጠሪያ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

### 11. የፌደራል ፖሊስ ኃላፊነት

የፌደራል ፖሊስ በጉምሩክ አዋጅ የተጣለበት ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

1. ከጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያዎች፣ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና የመግቢያና መውጫ በሮች በሚደርሰው መረጃ መሠረት በባለሥልጣኑ የተላላፊነት ፈቃድ



120

ተሰጥቷቸው የሚተላለፉ ዕቃዎችንና ማጓጓዣዎችን ከጉምሩክ ትራንዚት መነሻ ቦታ እስከ መድረሻ ቦታ ለመቆጣጠር የሚያስችለውን መርሐ ግብር ያዘጋጃል፤

2. በተዘጋጀው መርሐ ግብር መነሻነትም በየዕለቱ በዋናነት ከአዲስ አበባ አዳማ፣ ከአዳማ- አዋሽ፣ ከአዋሽ- ሚሌ እና ከሚሌ- ጋላፊ ያለውን ርቀት በመቀያየርና በመቀባበል የሚሸፍኑ የፓትሮል ተሽከርካሪዎችንና ስኳዶችን ያሰማራል፣ የተጠናከረ የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፣ በሌሎች የመተላለፊያ መስመሮችም ተመሳሳይ ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፤

3. በመተላለፊያ መስመሮች ላይ የጉምሩክ ተላላፊ ዕቃዎች ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀምን ተላልፈው በፓትሮሊንግ ሥኳድ የሚያዙ ማጓጓዣዎችን እና እቃዎችን ከመቆጣጠሪያ ጣቢያዎችና ከቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ጋር በመቀናጀት ዕቃውን ከነማጓጓዣው አጅቦ የጉምሩክ ትራንዚት መድረሻ ቦታ ያደርሳል፤ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ለመውሰዱም ይከታተላል፤

4. ከዋናው መንገድ የሚወጡትንና ባልተፈቀደላቸው ቦታ የሚቆሙትን ማጓጓዣዎች አጅቦ ለሚቀጥለው ጣቢያ ያስተላልፋል፡፡

5. የፌዴራል ፖሊስ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ተግባራት እንደ አግባብነታቸው የክልል የፀጥታ ወይም ህግ አስከባሪ አካላትን በማሳተፍ ሊያከናውን ይችላል፡፡

## 12. የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት አስፈፃሚው ግዴታ

ማንኛውም ዕቃ የማስተላለፍ ሥራን የሚያካሂድ ሰው ተላላፊ ዕቃው በባለሥልጣኑ በተፈቀደው የጊዜ ገደብ እና በተላከበት ሁኔታ ውስጥ በጉምሩክ ትራንዚት መድረሻ ቦታ ካልደረሰ በስምንት የሥራ ሰዓት ውስጥ ለባለሥልጣኑ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

## 13. የማጓጓዣ ኃላፊው ግዴታ

ማንኛውም የማጓጓዣ ኃላፊ፡-

1. ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳይሰጠውና የጉምሩክ ሹም በሥፍራው ሳይኖር ወደ ሀገር የሚገባን ወይም ከሀገር የሚወጣን ተላላፊ ዕቃ እና ማጓጓዣ ከተወሰነው የጉምሩክ ወደብ ወይም የመተላለፊያ መስመር ውጪ ማንቀሳቀስ፣ ማቆም፣ ዕቃ መጫን ወይም ማራገፍ፣ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንኛውንም ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲጠጋ መፍቀድ፣ ወይም ማሳፈር፣ የጉምሩክ



121

እሽጐችን መፍታት፣ ማላቀቅ፣ መሥበር ወይም መቀየር ወይም እነዚሁ ህገ-ወጥ ተግባራት በሌሎች ሰዎች እንዲፈፀሙ ማድረግ የተከለከለ ነው።

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው ቢኖርም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም ማጓጓዣው ከተወሰነው የጉምሩክ ወደብ ውጪ ሊቆም ይችላል። ይሁን እንጂ ይህንኑ ሁኔታ በአቅራቢያው ለሚገኝ ጽ/ቤት ወይም ሕግ አስከባሪ አካል በ24 ሰዓት ውስጥ ሪፖርት ማድረግ አለበት።

## ክፍል አራት
## ቅጣቶች

### 14. በባለስልጣኑ እና በፌዴራል ፖሊስ ላይ የተጣሉትን ግዴታዎች ባለመወጣት ስለሚኖር ተጠያቂነት

ማንኛውም የባለሥልጣኑ መስሪያ ቤት የመቆጣጠሪያ ጣቢያ፣ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት፣ የመግቢያና መውጫ በር ሠራተኛ ወይም ሹም ወይም የፌዴራል ፖሊስ አባል በዚህ መመሪያ የተጣለበትን ኃላፊነት ባለመወጣት ጥፋት ፈጽሞ ሲገኝ በየመስሪያ ቤቶቹ የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ የሚወሰደው የዲሲፕሊን እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ በአዋጁ አንቀጽ 89 እና 90 ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል።

### 15. ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ የሚያስከትለውን ግዴታ ስለመጣስ

ማንኛውም ዕቃ የማስተላለፍ ሥራ የሚያካሄድ ሰው ወደ ሀገር የሚገባ ወይም ከሀገር የሚወጣ ተላለፊ ዕቃ በተፈቀደለት የመተላላፊያ መንገድ ላይ ለሚገኝ ወይም መተላለፍ ለሚያበቃበት የጉምሩክ ጣቢያ በዚህ መመሪያ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መድረሱን በወቅቱ ያላሳወቀ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 103 ድንጋጌ መሠረት ከብር 5000 እስከ ብር 20000 ተቀጥቶ ፈቃዱ ይሰረዛል።

### 16. የመጓጓዣ ኃላፊ ግዴታዎችን ስለመጣስ

1. ማንኛውም የመጓጓዣ ኃላፊ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲጠጋ ካደረገ ወይም ከተፈቀደለት የጊዜ ገደብ ዘግይቶ ከደረሰ ወይም ማጓጓዣው እንዲንቀሳቀስ በጉምሩክ ከተፈቀደ በኋላ ምክንያቱን ለጉምሩክ ሳያሳውቅና ፈቃድ ሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ በአዋጁ አንቀጽ 101(1)



122

ላይ በተመለከተው መሠረት ከብር 2000 እስከ ብር 5000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል።

2. ማንኛውም የማጓጓዣ ኃላፊ ጉምሩክ ወደብ በደረሰ ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ዕቃ የጫነ ወይም ያራገፈ ወይም ለመጫን ወይም ለማረጋፍ ሙከራ ያደረገ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 101(2) መሠረት ከብር 7000 እስከ ብር 10000 በሚደርስ መቀጫ እና ከ5 እስከ 7 ዓመት በሚደርስ እስራት ይቀጣል።

3. ማንኛውም የማጓጓዣ ኃላፊ ወደ ሀገር የሚገባ ወይም ከሀገር የሚወጣ ተላላፊ ዕቃን ከጉምሩክ ወደብ ውጭ ያራገፈ ወይም የጫነ ወይም ለማራገፍ ወይም ለመጫን የሞከረ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 101(3) ላይ በተደነገገው መሠረት የዕቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር 7000 እስከ ብር 10000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ7 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።

4. ማንኛውም የማጓጓዣ ኃላፊ የዕቃ መተላለፊያ ሰነድ (የመንገድ ወረቀት) የሰረዘ፣ የደለዘ፣ ወደ ሐሰት የለወጠ ወይም በሰነዱ ላይ ተገቢ ያልሆነ ድርጊት የፈፀመ እንደሆነ በአዋጁ አንቀጽ 93 /1/ሐ መሠረት ይቀጣል።

17. <u>እሽጎችን በለመፍታት</u>

1. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ ፈቃድ ሳያገኝ፡-
   ሀ. በመተላለፍ ላይ ባሉ ወይም የጉምሩክ ወደብ በደረሱ ማጓጓዣዎች ወይም ዕቃዎች ላይ የተደረገውን የጉምሩክ ማሸጊያ የፈታ ወይም የቆረጠ ወይም ያላቀቀ እንደሆነ፣ ወይም
   ለ. በዕቃው ወይም በዕቃው መያዣ ላይ የተደረገውን ምልክት ያነሳ፣ የፋቀ፣ የሰረዘ ወይም የለወጠ እንደሆነ፣ ወይም
   ሐ. ማሸጊያውን ወይም መያዣውን ከፍቶ ወይም ሰብሮ አንዱን ዕቃ ከሌላው የደባለቀ፣ያጐደለ፣ የጨመረ እንደሆነ፣

   በአዋጁ አንቀጽ 95(1) ላይ በተደነገገው መሠረት ከብር 5000 እስከ ብር10000 በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ እና ከ7 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት ይቀጣል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ድርጊት የተፈፀመው ኃይል በመጠቀም ወይም በቡድን በመደራጀት ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 95(2) መሠረት የፅኑ እሥራቱ ከ10 እስከ 15 ዓመት ከፍ ይደረጋል።

Federal Democratic Republic of Ethiopia Revenues and Customs Authority



123